ሃይማኖትና ወጣቶች

«በወጣትነትህ ወራት ፈጣሪህን አስብ፡፡» መክ ፲፪ ፡፩

አንዳንድ ወጣቶች ከእምነት መጻሕፍት በወጣ መልኩ የእግዚአብሔር መኖር የሚያረጋግጡ ማስረጃዎችን ይጠይቃሉ፡፡ አንዳንዶቹ ደግሞ እንስሳ የለመለመ ሳርን አይቶ እንደሚበላ፤ እንዲሁ ማስረጃ መታየትና መዳበስ አለበት ይላሉ፡፡ ነገር ግን ሰዎች የእንስሳት ባሕርያት ብቻ ያሏቸው አይደሉም፡፡ የማሰብ ችሎታ ስላላቸው አእምሮአቸው የሚያቀርብላቸውን ማስረጃ ሊጠቀሙበት ይችላሉ፡፡ ለምሳሌ ሰው የሙዚቃን አስደሳችነትና የሥዕልን ቁንጅና የሚረዳውና የሚገነዘበው በአእምሮ ነው፡፡ እንስሳ ግን የሙዚቃን ድምጽ ሰምቶ ወይም ሥዕልን ተመልክቶ መመሰጥ እንኳን አይችልም፡፡

ታላቁ የግሪክ ፊላስፋ ሶቅራጥስ በተፈጥሮ ምርመራ የነፍስንና የእግዚአብሔርን መኖር አረጋግጧል፡፡ ከእምነት መጻሕፍት ውጭ የእግዚአብሔርን መኖር የሚያመለክቱ ዋና ዋናዎቹ ማስረጃዎች ቀጥሎ ያሉት ናቸው፡፡

፩ ፥ ምንጭ (አስገኝ)፡፡ ጠፈር በውስጡ ያለውን ሁሉ እንደያዘ እራሱን አስገኝ ሊሆን አይችልም፡፡ በዓለም ውስጥ የሚታየው እንቅስቃሴ የመጀማሪያውን አንቀሳቃሽ ያመለክታል፡፡ በግልጥ የሚታየው ያጌጠው ሰማያዊና ምድራዊ መልክ ፤ በዓመታትና በወራት፤ የተከፈሉት ክፍለ ጊዜያት ሰዓሊን ያመለክታሉ፡፡ የዓባይ ድልድይ ወይም የእጅ ወይም የጠረጴዛ ሰዓት ትክክለኛ ውን ጊዜ በመጠበቅ ያለ አንድ ሠሪ እንደማይገኙ ሁሉ ጠፈርም የለውን ሥርዓትና ሕግ ይዞ ሊገኝ አይችልም፡፡ እንዲሁም እግዚአብሔር ባይኖር ኑሮ ወጣቶች ህላዌውን ለመከራከር ባልሞከሩም ነበር፡፡

፪ ፥ ጠቅላላው የዓለም ሰዎች አስተሳሰብ የእግዚአብሔርን ህላዌ ያመለክተናል፡፡ በዚህ ቋሚ ዓላማ ላይ ጠቅላላው የዓለም ፍርድ ሊሳሳት አይችልም፡፡ ሰዎች ሁሉ በተፈጥሮ የእግዚአብሔርን መኖር እንዲያምኑ የእግዚአብሔር እጅ ማኅተም በፍጥረቱ ላይ ታትሟል፡፡ እግዚአብሔር መኖሩን ለመገንዘብ ሰዎች እራሳቸውን ሊገፋፋና ሊያባብሉ አያሻቸውም፡፡ እግዚአብሔር አለመኖሩን ለማረጋገጥ እራሳቸውን ለማሸነፍ ይሞክራሉ፡፡ እስካሁን ድረስ ማንም ሰው ቢሆን እራሱን በማስገደድ እግዚአብሔር ላለመኖሩ ቋሚ ምክንያት ያገኘ የለም፡፡ የእግዚአብሔርን መኖር በቀላሉ መጨበጫ ባለው ማስረጃ ለማረጋገጥ ባይችልም ላለመኖሩም የተሰጠ ማስረጃ አናገኝም፡፡ ሰዎች የእግዚአብሔርን ህላዌ ለመቀበል ከማዘንበል ይልቅ ወደ ተቃራኒው ያዘነብላሉ፡፡ እግዚአብሔር የለም ብለን ምናልባት ያለ እንደሆነ እንዳንጠየቅ አለ ማለት የለም ከማለት የተሻለ ነው የሚለው አገጋገር ንጹሕና ትክክለኛ አስተሳሰብ ነው፡፡

፫ ፥ የእግዚአብሔርን ህላዌ ሞራላዊ ኅሊና ያረጋግጣል፡፡ በማንም ሰው ዘንድ የክፉና የደግ ስሜቶች አሉ፡፡ ሰው ክፋ ሲያደርግ በልቡ ውስጥ ይሰማዋል፡፡ አንዳች ነገር አድራጐቱን ይዘልፈዋል፤ ከውስጣዊ ድምጽ ውጭ እንደሄደ ያውቃል፤ ይህ እኛ ያልሠራነው ወይም ሌሎች ሊሠሩት የማይችሉት የኅሊና ድምጽ ነው፡፡ የምናደርገውን ነገር ሌሎች ቢያውቁብንም ወይም ባያውቁብን ውስጣዊው ድምጽ መቃወሙን አያቋርጥም፡፡ ይህ ድምጽ ከመሳሳታችን በፊት በማስጠንቀቅ፤ ከተሳሳትንም በኋላ በመውቀስ ሁልጊዜ ልናደርገው ከምንፈልገው ጋር አይስማማም፡፡ ይህ በኅሊና የተነገረው ሕግ በልቦናችን ላይ የጻፈውን ሕግ ሰጭ ያስታውሰናል፡፡

፬ ፥ እንዲሁ ደግሞ ፍርድ የሚገባው ነገር እግዚአብሔር እንዳለ ያስገድደናል፡፡ በሰዎች ዘንድ ያለው ትክክለኛ ፍርድ ፈራጅ እግዚአብሔር እንዳለ ያመለክታል፡፡ ይህ ያለን ፍርድ እኛው እራሳችን ለራሳችን የሰጠነው ፍርድ አይደለም፤ እኛን ከፈጠረ የመጣ ነው፡፡ ማንም ቢሆን የሌለውን ሊሰጥ አይችልም፡፡ ፍርድ በዚህ ዓለም ላይ በሰዎች ላይ ሊሠራ አይቻልም፡፡ በዚህ ዓለም ደግ ሁልጊዜ ሲሠቃይ ክፋ ይበለጽጋል፡፡ ስለዚህ የሰው ፍርድ ሚዛኑን ሊጠብቅ አልቻለም፡፡ በዘላለማዊው አምላክ አንድ ቀን ፍርድ እንደሚሰጥ ግን እናምናለን፡፡ የሃይማኖት መጻሕፍት የእግዚአብሔርን መኖር ለመፈለግ የተጻፉ መጻሕፍት ሳይሆኑ እኛ በእግዚአብሔር ኃይል እርስ በርሳችን እንዴት እንድናኖር የሚያመለክቱ ናቸው፡፡

ክህደት ደስታንና ምኞትን በነጻ ለመፈጸም እንዳያመች የተፈጠረ ጉዳይ ነው፡፡ በሌላ መልክ ደግሞ ባለማስተዋልና ጥበብን ባለማግኘት ነው፡፡ ልበ አምላክ ዳዊት እንዲህ አለ «ሰነፍ በልቡ አምላክ የለም ይላል»፡፡ መዝ. ፲፬ ፡ ፩ «በዚያን ዘመን ያለ ክረስቶስ ነበራችሁ፤ ከእሥራኤልም ሥርዓት ልዩ ነበራችሁ ከተስፋውም ኪዳን ፤ ተስፋም አልነበራችሁም በዓለምም ያለ አምላክ ነበራችሁ» ኤፌ. ፪ ፡፲፪፡፡ ስለዚህ ክህደት የሌለና ሰውም ሊቀበለው የማይቻል እንግዳ ነገር ነው፡፡

ሃይማኖታችንን ካላወቅን ማኅበራዊ ኑሯችንን ለማወቅ አንችልም፡፡ ሃይማኖት ማኅበራችንና እያንዳንዳችንን የሚያሳድግ ነው፡፡ ሥቃይ እንዲጠፋ ፍቅርና ወንድምነት በሃይማኖት ሊገለጥ

ይገባዋል። ሕይወታችን ሥርዓት ያለውና የተደራጀ እንዲሆን የሚረዳን ሃይማኖት ነው። በዚህ ዓለም በሚደርስብን ሥቃይ ሁሉ የሚቀጥለውን ተስፋ በማድረግ እንጽናናለን አብረን አምልኮታችንን ስንፈጽም ፤ ስንጸልይ፤ ስንዘምር፤ መሥዋዕት ስናቀርብ፤ የሚያጽናናን የክርስትና እምነታችን ነው።

እያንዳንዳችን የምንሳሳትባቸውና ከማደግና ከእርምጃችን የሚያስቀሩን ነገሮች በብዛት ይገኛሉ። ለምሳሌ ፤ የቁማር ጨዋታ፤ መስከር፤ ከቤተክርስቲያን መራቅ፤ ሥራ አስፈች መጻሕፍትን ማንበብ፤ በጠባያቸው የጠፋትን ወጣቶች መጐዳኘታችን፤ ዛሬ ልንሠራው የምንችለውን ነገር ለነገ ማዘግየታችንና ይህን የመሳሰሉት ናቸው።

በዕውቀት የሚበልጡንን ሰዎች ምክር አለመቀበላችን፤ የነበረንን ሳንቆጥብ ቀርተን መደኸየታችን፤ ክርስቶስን በወጣትነታችን አለማወቃችን ናቸው።

ክርስቶስንና ያስተማረውን ትምህርት በወጣትነታችን ብንረዳ ከብዙ ኀዘንና ከአያሌ ጥፋት እንድን ነበር። «ሰው በታናሽነቱ ቀንበር ቢሸከም መልካም ነው ።» ሰቆ. ኤ. ፫፡ ፲፯

«የጭንቅ ቀን ሳይመጣ፡ በወጣትነትህ ወራት ፈጣሪህን አስብ፡ ደስ አያሰኙኝም የምትላቸው ዓመታት ሳይደርሱ፤» መክ. ፲፪፡፩. እግዚአብሔር ወጣትነታችንን ካጠወለገ በኋላ ልንቀርበው አንችልም፤ ኦውግስጢኖስ «አምላኬ ሆይ ምነው በሕፃንነቴ ዐውቄህ በነበር» ይላል። ስለዚህ ነው ብዙዎች ቅዱሳን እራሳቸውን ለእግዚአብሔር የሚቀድሱት። ምክርን አሁኑኑ በርካሽ ዋጋ ካልገዛን ወደፊት በውድ ዋጋ እንገዛለን። በወጣትነታችን ልቦናችንን ለእግዚአብሔር ብንሰጥ በሽምግልና ጊዜ ጠንካሮች እንሆናለን። የወጣትነት ዘመን የኃይልና የንቃት ዘመን ነው። የነፍሳችን ቆራጥነት የሚፈለግበት ነው። ስለዚህ እግዚአብሔርን ለመፍራትና ለመከተል የተሻለውና የተመረጠው ጊዜ አሁን ነው። በወጣትነቱ ሃይማኖተኛ የሆነ ክፋ ዘመን ከመምጣቱ በፊት ይድናል። ዛሬ ብዙዎችን ወጣቶች እንደምናያቸው ስለሃይማኖት አይጠነቀቁም። ስለፖለቲካ እምነት እንደሚከራከሩና ስለ ሌሎችም ዕውቀቶች እንደሚያስቡ ሁሉ ለሃይማኖትም ሊጠነቀቁ ያሻል። ሃይማኖት፤ ቤተክርስቲያን እግዚአብሔር ፤ ጸጋ መንፈስ ቅዱስ የሚባሉ ነገሮች እንዳሉ የማያስቡ ይኖሩ ይሆናል። ስለ ትምህርታችን ፤ ስለ ሥራችን ስለ ወደፊት ዕድላችን፤ የምንጠነቀቅ ከሆነ የሃይማኖታችንን ጉዳይም ልናስብበት ይገባል።
መጀመሪያ የእግዚአብሔርን መንግስትና ጽድቁን መፈለግ አለብን። መጽሐፍ «አድሮ ለሚጠፋው መብል ሳይሆን ዘለዓለም ለማይጠፋው ሕይወት ሥሩ።» ይላል ዮሐ ፮ ፳፯ ። ሰው በገንዘቡ ብዛት በሰውነቱ ኃይል ከፍተኛነት ወይም በዕውቀቱና በማኅበራዊ አቋሙ አይመዘንም። ይህ ሁሉ ሰውን እውነተኛ ሰው አያደርገውም። ነገር ግን «የጥበብ መጀመሪያ እግዚአብሔርን መፍራት ነው» እንደተባለው የሰው አቋም የሚገለጸው በሃይማኖታዊነት በመልካምነትና በቅዱስነት ነው።

ሃይማኖት ወጣቶችን ተሸክሞ ያኖሣቸዋል፤ ሃይማኖት ያሸመግላል፤ ሃይማኖት ለተማረ ሰው ጌጡ ነው፤ ለሰው የደስታን ጐዳና የሚጠርግ እርሱ ብቻ ነው። በእምነት ሰላም የሕይወት ፍጹምነት ይገኛል «ሥጋዊ ነገር ማድረግ ለጥቂት ዘመን ይጠቅማልና፤ አምልኮት ግን በሁሉም ይረባል። ለእርሱም ተስፋ አለው፤ በዚህ ዓለም ሕይወት በሚመጣውም ደግሞ» ፩ኛ ጢሞ፬፡፰ መልካም ይሆንልን ዘንድ እግዚአብሔር ያዘዘንን ሕጉንም ልንጠብቅ ይሻል፡ ክርስቶስ ወጣቶችን በፍቅር መልክ እየተመለከተ ሊያድናቸው ይጥራል፡ ወደ እርሱ ተመልክተን ስጦታውን እንቀበል። ሃይማኖት ማለት እንደንድ የተዘክሮ ድርጊትን ማድረግ ብቻ አይደለም። ክርስትና ማለት ክርስቶስን መከተል ተገቢውን ለውጥ ማድረግ በጐና መልካሙን ምግባር ማሳየት ሰብአዊነትን ማገንዘብ በልቦናችን ያለውን በሽታ መጣል ማለት ነው፤ ኃጢአት በውስጣችን ጸድቋል መጀመሪያ ውስጣችን ሊነጻና ሊፈወስ ይገባል። «ሁሉ በክርስቶስ አዲስ ነገር ይሁን አሮጌው ፈጽሞ ይሂድ ሁሉ ይታደስ» የክርስትናን ትምህርት ብንቀበል ሁሉ ይታደሳልና እኛም እንደሰታለን ፤ ወጣቶች የእግዚአብሔር መኖር በልቦናችሁ ውስጥ ይኑር፤ በኋላ ሕይወት ጥበብ፤ ጽድቅ፤ ቅድስና፤ ድል፤ ተስፋ ደኅንነት ፤ ኃይል ይሆናችኋልና።

ይቆየን።

ቀሲስ ሰሎሞን ሙሉጌታ
መስከረም 21፡ 2001 ዓ. ም.